## የወቅቱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ፥ ማህበራዊ፥ ኢኮኖሚያዊ፥ ዲፕሎማሲያዊና ሌሎችም ተዛማጅ ሁኔታዎች

## ክፍል አራት

በክፍል ሶስት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቆመናል የሚሉ ተቃዋሚ ድርጅቶችን በተመለከተ ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ጉልህ የፈተና ወቅት መሆኑንና ከምንም በላይ በራስ መተማመንና የሃገሪቱን ሉዓላዊነትና የሕዝቧን አንድነት መሰረት ባደረገ መርኅ ስር የመሰባሰብን አስፈላጊነትና አጣዳፊነት እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ዛሬም እንደትናንቱ ለጋራ ሃገራችን በጋራ ለመስራት እንነሳ የሚለውን ጥሪውን ከፍ አድርጎ እንዳሰማና ምላሹንም እየተጠባበቀ ስለመሆኑ ገልፀናል፡፡
የክፍል ሶስት ዝግጅታችን ዛሬ በሕወኃት/ኢሕአዴግ ሙሉ ቁጥጥር ስር የዋለው የኢትዮጵያ የወቅቱ ኢኮኖሚ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለመተንተን በክፍል አራት የኢትዮጵያ ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታ ለመገናኘት ቀጠሮ ይዞ ነበር የተደመደመው፡፡

ኢትዮጵያ ሃገራችን ከሕዝብዋ ሦስት አራተኛው ከእጅ ወደ አፍ የሚሆን ምርት ብቻ በሚያገኝባቸው ትንንሽ እርሻዎች ላይ ነው ሕይወቱ የተንጠለጠለው፡፡ ኢኮኖሚው አስተማማኝ ባልሆነው ዝናብ ላይ በተመረኮዘ እርሻ ላይ የተንጠለጠለ ከመሆኑም በላይ እንደቡና ባሉ ዋጋቸውን ባዕዳን ባሻተው በሚገመዳድልባቸው ምርቶችም ላይ ነው ኢኮኖሚያችን የተመረኮዘው፡፡ሀገራችን ውስጥ ድርቅ በመጣ ቁጥር ወይንም የዓየሩ ባኅሪ በተለወጠ ቁጥር ብዙ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ለረሃብ፥ ችጋርና ዕልቂት ይዳረጋሉ፡፡ ህወሃትና ደጋፊዎቹ በሚቀፈቅፉት ስሌት እንኳን ሕይወቱ እንዲያጥር በጅምላ የተፈረደበት ይመስል ዛሬ አንድ ኢትዮጵያዊ በአማካይ ለመኖር የሚችለው 42 አመት ብቻ ሆኗል (ከአንድ እ. አ. አ በ 2003 አ. ም በተደረገ ጥናት መሠረት)፡፡ የህወሃት መንግሥት ስልጣን ከመያዙ በፊት አንድ ኢትዮጵያዊ በአማካይ 47 አመት ሊኖር እንደሚችል ነበር የሚነገረው፡፡ በአምራችነት ሊሠለፉና ራሣቸውን ችለው ሊኖሩ በሚያስችላቸው የዕድሜ ክልል ከሚገኙት ዜጎች ከፊሉ ማለትም ግማሽ የሚሆኑት ብቻ ናቸው የሙሉ ጊዜ ሥራ ያላቸው፡፡ ቀሪዎቹ በአመርቃኙ የሥራ እጦት ባይሰናከሉ ኖሮ ከእራሳቸው አልፈው ሀገራቸውንም ሊጠቅሙና ሊያሻሽሉ በቻሉ ነበር፡፡ የሕዝቡ ብዛት እየጨመረ ሲሄድ ሁሉም የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት መስፈርቶች እያሽቆለቆሉ በመሄድ ላይ ናቸው፡፡ የእርሻም ሆነ የኢንዱስትሪ ምርቶች ዝቅተኛ ናችው፡፡

ሀገሪቱ ወደ ውጭ ከምትልካቸው -ዕቃዎች ሽያጭ የምታገኘው ገንዘብም አነስተኛ በመሆኑ ከውጭ መግዛት ያለባትን ለልማትና ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች ለማስመጣት የሚያዳግታት ሁኔታ ነው የተፈጠረው፡፡ ስለሆነም ኢትዮጵያ በውጭ እርዳታ ላይ ጥገኝነትዋ ከማንኛውም ጊዜ የባሰ

ሆኗል። ኢትዮጵያ የምታገኘው የውጭ ርዳታ እ. አ. አ. በ1970 ዓ ም ከጠቅላላው የሀገሪትዋ የዓመት ምርት (ጂ.ዲ.ፒ.) ከ 1 በመቶ ያንስ የነበረው ዛሬ ወደ 15 በመቶ ደርሷል። እ.አ.አ. በ 2001 ከመንግስት መደበኛ ወጭ 39 በመቶ የሚሆነው ከውጭ ርዳታ የተገኘ ነበር። እ. አ. አ. በ2002/2003 በአይ. ኤም. ኤፍ እና በሕወኃት/ኢሀአዴግ መንግሥት የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒሥቴር በተጠናቀረ ስሌት መሠረትየሀገሪቱ ጠቅላላ የዓመት ምርት (ጂ.ዲ.ፒ.)

1. እርሻና ተዛማጅ የሆኑት የኢኮኖሚ እንቅሥቃሴዎች ...... 39.4 ከመቶ
2. ኢንዱስትሪ ...................................................... 11.9 ከመቶ
3. አገልግሎቶች ..................................................... 48.7 ከመቶ ነበር።

ይህ የተጠቀሰው አኃዝ የሀገሪቱን ጠቅላላ የዓመት ምርት (ጂ.ዲ.ፒ.) ምንጮች የሚያሳየው ሠሌዳ ሀገራችን ውስጥ የኢንዱስትሪው ድርሻ አሁንም ዝቅተኛ መሆኑንና በተለይም የአገልግሎት ክፍለ ኢኮኖሚ እያላደገ የመጣ ሥፍራ መያዙን ነው። የማከፋፈያ አገልግሎት ሰጭ የሆኑት እንደ ንግድ፥ ሆቴሎችና ሬስቶራንቶች፥ መጓጓዣና መገናኛ ዓይነቶቹ ናቸው ከ1996/97 እስከ 1999/2000 ባሉት ጥቂት ዓመቶች ውስጥ በ24 ከመቶ አድገዋል የተባሉት። ይህች ከደሆችም ደሀ የሆነችው ኢትዮጵያ ውስጥ ለልማት ሳይሆን ለጥፋት ይውል የነበረው በተለይም ለአስተዳደርና "ለሀገር መከላከያ" እየተባለ ይወጣ የነበረው ገንዘብ መጠን ደግሞ በ69 ከመቶ ነበር ያደገው። አቶ መለሰ ዜናዊና አቶ ኢሣያስ አፈወርቂ ለአያሌ ዓመቶች ያናውዛቸው የነበረው ፍቅራቸው አልቆ አፍነው የያዙትን ሕዝብ ወደ ጦርነት የማገዱት በዚሁ ወቅት ስለነበረ ለውትድርና ይወጣ የነበረው የገንዘብ ወጭ ያለጥርጥር ከተገለጠውም የበለጠ እንደሆነ ይገመታል። ለአብነት በዚሁ ወቅት በአጠቃላይ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ ጤናማ አለመሆኑን የሚያመለክቱ ጥናቶች እንዳመለከቱት
1.የሀገር ውስጥ ምርት (ጂ.ዲ.ፒ.) ዕድገት በፐርሰንት ..... ኔጋቲቭ 3.8
2.የሸመታ ዋጋ ግሽበት (ኢንፍሌሽን) በፐርሰንት ................... 14.6
3.ወጭና ቀሪው ሲመዛዘን በመንግሥት እጅ የሚቀረው ገንዘብ ወይንም ዕዳ (የአሜሪካ ዶላርስ፥ በሚሊዮኖች) ..................ኔጋቲቭ 397
4.ወደ ውጭ ከተላኩ የንግድ ዕቃዎች ሽያጭ የተገኘ ገንዘብ (የአሜሪካ ዶላርስ፥ በሚሊዮኖች) ..................................... 468
5.ወደ ሀገር ውስጥ በግዥ ለገቡ ዕቃዎች የወጣው ገንዘብ (የአሜሪካ ዶላርስ፥ በሚሊዮኖች) ..................................... 1976
መሆኑ ሲታወቅ በዚሁ ወቅትና ከዚያም በፊት በነበሩት ሁለት ዓመቶች የሕዝባችንም ብዛት 70 ሚሊዮን ደርሷል ይባል ነበር።

*<u>ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት ኢኮኖሚያችንን ከሚገልጡት አሃዞች ስንነሣ በዚያን ጊዜ ማለትም ከሁለት ዓመቶች በፊት የነበረው የኢኮኖሚ ዕድገት ሣይሆን የከፋ መቆርቆዝ ማለትም የኋሊት ጉዞ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ከዚያ በኋላ ያለው ሁኔታ ደግሞ የተባባሰ ይሆን እንደሆነ እንጂ የተሻለ ይሆናል ለማለት የሚያስችለን ምንም መረጃ የለም፡፡</u>*

*ስለሆነም ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ አሉታዊ ክስተቶች መከሰታቸው በሀገሪቱ ላይ ከፍተኛ ውድቀት እያደረሱ መሆናቸውን ነው ዛሬ ልንገነዘብ የሚገባ፡፡ ከተፈጥሮ የዓየር ሁኔታ መዛባትና ሀገራችንም ካለችበት ጂዎግራፊያዊ አቀማመጥ ጋር ተያይዞ ደጋግሞ የደረሰብን ድርቅ፤ ኤች. አይ. ቪ. /ኤይድስ የተባለው ቀሣፊ ወረርሽኝ፤ የወባ ወረርሽኝ፤ የበረሃ አምበጣ ወረራ፥ የማያባሩ ጦርነቶች፤ ለኅዝብ ደንታ የሌላቸውና አምባገነናዊ መንግሥቶች፤ ስደት በተለይ ደግሞ የተማረው የሰው ሃይል ፍልሰትና ሌሎችም ያልጠቀስናቸው ስር ሰደድ ችግሮች ዛሬ መታወቂያዎቻችን ከሆኑ ውለው አድረዋል፡፡ እኒህ ችግሮች መንግሥታዊም ሆነ ሌላ ሃይል ሳይቋቋማቸው ተጋግዘው ከባድ ጥፋት፥ አንዳንዴም መልሶ በፊት የነበሩትን እንደወትሮአቸው ለማድረግ በማይቻል ደረጃ ነው ሀገሪቱን እያወደሙ የሚገኙ፡፡*

*ከ40 ዓመት በፊት የኢትዮጵያ ምድረገጽ 44 ከመቶው፥ ከ 30 ዓመት በፊት ደግሞ 25 በመቶው የሚሆነው በደን የተሸፈነ ነው ይባል ነበር፡፡ አሁን ደን የለበሰው መሬትዋ ከ 3 ከመቶ በታች እንደሆነ ነው የሚነገረው፡፡ በእርግጥም ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ደን አለአግባብ ተመንጥሮ ወይንም እየተለበለበ፥ እየደረቀ፥ እየተነገለ አልቋል፡፡ ከደኑ መመንጠርና ማለቅ ጋርም ስባት ያለው አፈር ወደአቧራነትና ደለልነት እየተለወጠ በነፋስ ሃይል በመብነን ወይንም ጎርፍ በመጣ ጊዜ እየታጠበ በጅረቶችና ወንዞቻችን ተጠራርጎና ተጭኖ (በደለል መልክ) በመወሰድ እሱም ልክ እንተሰደዱት ልጆችዋ ሀገሪቱን ጥሏት ድንበሯን እየጣሰ ይወጣል፡፡ በዚህ መንገድ ሰዉ ብቻ ሳይሆን ሊለማና ሊበቅልበት የሚችለው መሬትም ደህይቷል፡፡ የመሬቱ ስባት ወይንም ልማት ማጣት ደግሞ በተለመዱት የርሻ ኋላቀር ዘዴዎች በመጠቀም ከተወሰንን እያደገ የመጣውን ሕዝባችንን ለመመገብ አንችልም ማለት ነው፡፡ የዱር አራዊቶችዋና እንስሣቶችዋም መኖሪያና መሸሸጊያቸው የሆነው ደን ሲያልቅ አብረው ተመናምነዋል፡፡*

*የኢትዮጵያን በጣም እያደገ ያለ ሕዝብ በበቂ ለመመገብ የሚቻለው የሀገራችን የእርሻው ምርት በዚያው መጠን ሊጨምር ሲችል ነው፡፡ ለእርሻው ምርት እድገት እንዲገኝ ደግሞ አራሹ ሕዝብ በልቶ የሚያድር፥ ጤናማና የተማረም ሊሆን ይገባል፡፡ በተጨማሪ ሊያርሰው የሚችለው የራሱ የሆነ መሬት፥ ማለትም "የእኔ ነው፥ ማንም አይወስድብኝም፥ ልሸጠው፥ ለልጆቼ ላወርሰው እችላለሁ " ወዘተ ብሎ የሚንከባከበው መሬት፤ በግል ንብረትነት ደረጃ የራሱ የሆነ ማለት ነው፥ ሊኖረው ይገባል፡፡ በዝናብ ላይ ከመተማመን በመላቀቅ በመስኖ ወሀ ተጠቅመን ለማምረት መቻልም አለብን፡፡ የርሻውን ምርት ለማሳደግ የሚያስችሉ የርሻ ግባቶች አቅርቦት ሊኖር ይገባል፡፡ የርሻው ምርት  ዕድገት በርካታ የሥራ መስኮችን ሊፈጥር*

የሚችል እንዲሆን መታቀድም አለበት፡፡ ለነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች መሟላትና መገኘት ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ያለውን የመሬት ይዞታ በመለወጥ አርሶአደሩና ገበሬው ብዙ እንዲያመርት ይረዳል ተብሎ ስለሚታመን የመሬቱ ባለቤት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ለሁሉም ለሕዝባችን ሕላዌና ለአገራችን ሁለንተናዊ እድገት ቁልፍ የሆነውን የእርሻን ይዞታና የልማት እንቅስቃሴ በተመለከተ መሠረታዊ የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ በአፋጣኝ መደረግ አለበት፡፡ አገራችን የተጠናወታትን አመርቃዥ የሆነ የምግብ እጥረት አዙሪትንና በዚሁም ሳቢያ እያደገና ሥር እየሰደደም የመጣውን የተረጅነትና ጥገኛነት አሸማቃቂ ስነ-ልቦናዊ ተጽዕኖን ማስወገድ አስፈላጊ ብቻ ሣይሆን ያለ አንዳች ጥርጥር አጣዳፊም ነው፡፡
ለአሥራ አራት ዓመታት በሥልጣን ላይ ከቆየ በኋላ ዛሬም ነገም በየዓመቱ ይህን ያህል ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ለአስከፊ የምግብ እጥረት (የርሃብ የሙክሻ ስም መሆኑ ነው) እየተዳረጉ ነው ይለናል - ዓይን አውጣው የሕወሃት/ኢሕአዴግ መሪ፡፡ በተደጋጋሚ ዜጎቻችን ለመመገብ ካለመቻላችን ጋር ተያይዞ የመጣው የውጭ እርዳታን የመተማመን አዝማሚያ፥ ወይንም የተረጅነት ስነ-ልቦናዊ ዝግጅት፥ ጤናማ ያልሆነ ልማድን እያጎለበተ መምጣቱም በጣሙን የሚያሳዝንና የሚሳሰብም ጉዳይ ነው፡፡

አሁን በሀገራችን ውስጥ በሥራ ላይ ውሎ የምናየው የመሬት ይዞታ ፖሊሲ ለእርሻ ምርትና በግብርና ዙሪያ ለሚኖር የልማት እንቅስቃሴ ምቹ ካለመሆኑም በላይ ጎጅነቱ የሚያመዝን ሆኖ ነው የተገኘው፡፡ በተለይ አገራችን ካለችበት በተከታታይ ለበርካታ ዓመታት ሕዝቧን ለመመገብ አለመቻል ሁኔታ ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚራበውን ሕዝባችንን ሕይወት ለማዳን ሲባል የውጭውን ዓለም እርዳታ የመለመንና በሱም የመተማመን አሳፋሪ ልማድ ውስጥ በምትገኝበት ሁኔታ የመሬት ይዞታው ፖሊሲ ሊያስከትለው የሚችለው መዘዝ በአዲስ መልክ መታየቱ ተገቢ ነው፡፡ አሁን ባለው የመሬት ፖሊሲ በቂ የባለቤትነት ዋስትናና ማረጋገጫ ለአርሶአደሮችና በእርሻው ክፍለ-ኤኮኖሚ መሰማራት ለሚፈልጉ ሁሉ ስለማይሰጥና እነሱም ምንም ዓይነት ዘለቄታ ያለው አመኔታ በሚያርሱት መሬት ላይ ስለማይኖራቸው፥ ምርትን በሚያሳድጉ ግብአተ-ምርቶች ላይ ገንዘባቸውን ለማዋልም ሆነ በሌላ ተገቢ የእርሻው ልማት እንቅስቃሴ ላይ አቅማቸው የሚፈቅድላቸውን ሁሉ ለማድረግ አይደፋፈሩም፡፡ ግልጥ በሆነ የመንግሥት የመሬት ባለቤትነት ሥሪት ሥር በይዞታ የተሰጣቸውን መሬትም ቢሆን እራሳቸው እንዳሻቸው ማድረግ ስለማይችሉ፥ በየጊዜው ይዞታቸው ሊሸጋሸግ ወይንም ለሌላ ሊዛወር ስለሚችል፥ ለግል መሬታቸው ሊያደርጉ የሚችሉትን ያህል ተገቢ እንክብካቤ አያደርጉም፡፡ ስለዚህ አሁን በተግባር የሚውለው ገበሬውን የመንግሥት ጭሰኛ ያደረገ የመሬት ስሪት መለወጥ ይኖርበታል፡፡

በአጤቃላይ አሁን ያለው የመሬት ሥሪትም ሆነ፥

1.ለዘመናት እየተሸነሸኑ የመጡት የትናንሽ መሬቶች ይዞታ ሰፊና ዘመናዊ የእርሻ እንቅስቃሴ በማድረግ ምርትን ለማሳደግና አርሶአደሩንም ከራሱ ተርፎ ለሽያጭ ወደገበያ ለማቅረብ አያስችልም፡፡

2.ከመንግሥታዊ የመሬት ባለቤትነት ሥሪት ስር አርሶአደሮችና በእርሻ ልማት ላይ መሳተፍ የሚፈልጉ ባለሃብቶች የርሻ መሬቶቹ ባለንብረቶች ቢሆኑ ኖሮ ለመሥራት የሚችሉትን ያህል ለመሥራት አይደፋፈሩም፡፡ መሬቱ በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ሊወሰድባቸው ስለሚችል ሁሌም ከስጋት አይላቀቁም፡፡

3.ሀገራችን ውስጥ ያለው ዋነኛው ተፈጥሮአዊ ሃብት መሬት ሆኖ ሳለ፥ አርሶአደሮችና ሌሎችም በእርሻ ልማት ላይ መሠማራት የሚፈልጉ ወገኖች በሙሉ ልብ እንዲሠሩና የተሻለ አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ በርሻው መሬት ላይ በቂ የሆነ ሕጋዊ የባለቤትነት ዋስትና ሊኖራቸው ሲገባ፥ አሁን በሥራ ላይ ያለው ፖሊሲ ይኽን ዋስትና አይሰጥም፡፡ በመሆኑም ብዙ ቁጥር ያላቸው በውስጥም በውጭም ያሉ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ገንዘባቸውንና ዕውቀታቸውን በእርሻ ልማት እንቅስቃሴ ላይ ማዋል ሲችሉ ይህንን ከማድረግ ተቆጥበዋል፡፡ የርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ምርትም ዝቅተኛ እንደሆነ ነው ያለው፡፡

4.ከአገሪቱ ጠቅላላ ሕዝብ ሰማንያ አምስት በመቶ የሆነው በቀጥታ በአርሶ አደርነት፥ ተጓዳኝ በሆኑ የርሻ ሥራዎች ወይንም በርሻ ላይ በተመሠረቱ የኢኮኖሚ እንቅሥቃሴዎች ከሚያገኙት ምርትና ገቢ ነው የሚኖረው፡፡ ይሁንና 85 ከመቶ የሚሆነው ወገናችን በቀጥታ እያረሠውም ሆነ ለተዛማጅ የግብርና እንቅስቃሴዎች ያዋለው መሬት መጠን ከጠቅላላው ውስጥ በጣም አነስተኛው ክፍል ነው፡፡ ለመታረስና ለተዛማጅ የእርሻ ልማት ሊውል ከሚችለው የአገሪቱ መሬት ውስጥ ከመቶው አንድ እጅ ብቻ ነው፡፡ የመሬቱ ሥሪት፥ ማለትም መንግሥት የመሬት ባለቤት መሆኑ፥ የውሀ ሃብታችን አለመልማት ማለትም በአግባቡ በጥቅም ላይ አለመዋሉ (ለመስኖ ሥራና ለሃይል ማመንጨት ወዘተ አለመዋሉ )፥ ሊያርስ ከሚችለው የገጠር ኗሪ ሕዝብ ውስጥ በርካታው በተለያዩ እንደ ወባ ባሉ በሽታዎች በየጊዜው በተለይም በእርሻው ወቅት መጠቃቱ፥ የወጣት አርሶአደሮች በቂ ትምህርትና ዕውቀት አለማግኘት፥ አበረታችና አጋዥ ሕግና ደንብ፥ ምክር፥ ከእርሻ ሥራ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ግልጋሎቶችን አለማግኘታቸው፥ የርሻው መሬት መሸንሸን፥ የደኑ መመንጠርና የመሬቱ ስባት/ለምነት እየታጠበ የምርታማነቱ መቀነስ ያስከተለው አሳናፊነት ተስፋ አስቆራጭነት ... የቀረው መሬት ጦም አዳሪ እንዲሆን አስተዋጽዖ አድርገዋል፡፡

5.በልማት ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያስረዱት መሬትን ለመጠቀም የመቻል መብት መኖር በቂ እንዳልሆነና ግልጽ የሆነ የመሬት ባለቤትነት ሕጋዊ መረጋገጫና ዋስትና መኖር በጣም አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡

6.በገጠሮች የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን የመሬቶቻቸው ሕጋዊ ባለቤቶች ባለመሆናቸው የበርካታ ዓመቶች ሥራና እንክብካቤ የሚጠይቁት እንደ ዛፍ ተከላ፥ የቡናና የጌሾ ተክሎችን የማልማት ያሉት፥ የርከንና የግድብ ሥራዎችንም መሥራት ተደናቅፈዋል፡፡ የደን ውድመትንና የመሬቱን መራቆት ለመቋቋምና ለመቀልበስ አስቸጋሪ ሆኗል፡፡ በርከት ያለ ወጭ፥ ብዙ ጉልበት፥ ወይንም የረጅም ጊዜ እንክብካቤን የሚጠይቁ ከእርሻ ሥራ ዕድገትና ልማት ጋር የተያያዙ ወይንም አዳዲስ የመገልገያ መሣሪያዎችን ለማግኘት የሚደረጉ ጥረቶችንና እንቅስቃሴዎችን ከማድረግ የገጠሩ አምራች ሕዝብ ያለጥርጠር ተቆጥቧል፡፡

7.የመሬት ባለቤትነት የመንግሥት በመሆኑ መሬቱን በመንግሥት ጭሰኝነት የያዘው አርሶአደር በመሬቱ ዋስትና ብድር መበደርና ራሱንና አገርን በሚጠቅም የልማት ሥራ ላይ ለማዋል አይችልም፡፡ በደሃ አርሶአደርነት ዕድሜውን እንዲገፋ ይገደዳል፡፡ የሚያርሰውን መሬት በግል ባለቤትነት መያዝ ቢችል ማንኛውም በእርሻ ሥራ ላይ የተሰማራ መሬቱን በዋስትና በማስያዝ ለልዩ ልዩ የልማት ማጎልበቻም ሆነ ሌላ ጉዳይ አስፈላጊውን የሆነውን ገንዘብ ለመበደር በዋስትናነት ያገለግላል፡፡ በእርሻና በግብርናው ክፍለ-ኤኮኖሚ ላይ ማፍሰስና ማዋል ለሚፈልግ ሁሉ የሚያደፋፍርና የልማት እንቅስቃሴውን የሚያጎለብት ይሆናል፡፡

8.የመሬት ባለቤት መንግሥት በመሆኑ ገበሬው በቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረድ መጉላላትና መንገላታት ይደርስበታል፤ መንግሥታዊ አገልግሎቶችንም ሆነ ማናቸውንም ሕጋዊ መብቶች ከመንግሥት ጠይቆ እንዳያገኝና አጥብቆ እንዳይከራከር መሬት የመነጠቅ ማስፈራሪያ ስለሚደርስበት ገበሬው መንግሥት የሚፈልገውን እንዲፈጽም በማስገደጃ መሣሪያነት ይጠቀምበታል፤ መንግሥት ባሻው ጊዜ መሬትን ካልፈቀደው ቀምቶ ወይም ቀንሶ ለሌላ መስጠት ስለሚችል ገበሬው በረጋ መንፈስ ያለ መንግሥት ጣልቃ ገብነትና ስጋት ማረስ አይችልም፡፡

9.ምናልባት ከጥቂቶች የኑሮ ሁኔታቸው ከሚፈቅድላቸው በስተቀር፥ በርካታ፥ ኑሮአቸውን ለማቸነፍ ሲፍጨረጨሩ የሚኖሩ ዜጎች፥ የመሬት ባለቤት ባለመሆናቸው የአካባቢያቸውን የተፈጥሮ ሚዛን ለመጠበቅና የአየር ብክለትን ለመከላከል ተግተው እንዲሠሩ አይበረታቱም፡፡

እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት በገጠሩ የእርሻ መሬት ላይ የግል ባለቤትነት መብት አለመኖር ጋር የተዛመዱ ምክንያቶች በአጠቃላይ የገጠር ልማትንና በተለይ ደግሞ የእርሻ ልማት እንቅስቃሴንና የሕዝባችንን የማምረት፥ አምርቶም እራሱን የመመገብ አቅሙን ጎድተዋል፡፡

በዚህም የተነሳ ከእርሻው ምርት ዕድገት ጋር የሚያያዙትን በግብርና ውጤቶች ላይ የተመሠረቱ የአገሪቱን ኢንዱስትሪዎች፥ የርሻ ማዕከሎች በሆኑ አካባቢዎች ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ የቤቶች ሥራ እንቅስቃሴዎችን፥

የውጭ ንግድ አቅም መዳበርን፥ የዜጎች ጤና አጠባበቅን፥ በትንንሽ መንደሮችና አዳጊ ከተሞች ውስጥ የትምሕርት መስፋፋትን፥ የንጹህ ውሃ አቅርቦትን፥ የመገናኛ አውታሮች መዘርጋትንና ሌሎችንም የልማት ተግባሮችን በተዛማጅነት ለማሳደግና ለማሻሻል አልተቻለም።

የአርሶአደሩም ሆነ የማንኛውም በግብርና ለመተዳደር የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ የሚያርሰው መሬት ባለቤት የመሆንና የመሬት ባለቤትነቱም ዋስትና ሊኖረው ይገባል ስንል ሌሎችም ምክንያቶች አሉን። ዛሬ ሀገራችን ውስጥ አርሶአደሩ የመሬቱ ባለንብረትና ባለሙሉ መብትም አለመሆኑ በተለይ ለገጠሩ ገበሬ ዋነኛውን የማምረቻና የማንነቱም መሠረት የሆነውን ነገር ነው ያጣው። ይህ አርሶአደሩን ኢትዮጵያዊ በሚያርሰው መሬቱ ላይ ተስፋው እንዲቀጭጭ አስተዋጽዖ እንዳደረገ ሁሉ እያንዳንዱንም ዜጋ ከኅብረተሰቡ ጋርና ከአገሩም ጋር ያለውን መሠረታዊ ትስስር የሚያላላና የሚሸረሽር አደገኛ ጫና መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

እዚህ ላይ ዛሬ በሀገራችን ውስጥ ያለው የመሬት ሥሪት እንዳለ ሊቀጥል አይገባውም የሚል ሃሣብ የሚያቀነቅኑ ወገኖች የመኖራቸውን ያህል የመሬት ፖሊሲ መለወጥ የለበትም የሚሉ መኖራቸውንና መከራከሪያ ነጥቦችም እንዳሏቸው መግለፁ ጠቃሚ ነው።

1.የመጀመሪያው፥ በህወሃት/ኢሕአዴግም ጭምር ተደጋግሞ የሚነገረው የኢትዮጵያ አርሶአደሮች ያለው የመሬት ሥሪትና ፖሊሲ ተስማምቷቸው ተቀብለውታል የሚል ነው። ይህን ለማረጋገጥ ማመሣከሪያ ጥናቶቻቸውን ግን አያቀርቡም።

2.ለጥቀውም አርሶአደሩም ሆነ ማንኛውም በመሬት መጠቀም የሚሻ ሁሉ እስከፈለገ ድረስ የመሬቱ ተጠቃሚ ስለሚሆን ቁልፉ ጥያቄ የመሬት ባለቤትነት ሳይሆን ምርትን ለማሳደግ የሚያስችል መሬት በይዞታ ለማግኘት መቻሉ ነው ይላሉ።

3.ከዚያም ዛሬ ሀገራችን ውስጥ ባለው የመሬት ፖሊሲ አርሶአደሩና ማንኛውም የመሬት ተጠቃሚ ማድረግ የማይችለው የሚጠቀምበትን መሬት መሸጥ ብቻ ነው። አርሶአደሩ መሬቱን እንዳይሸጥና እንዳይለውጥ የተከለከለበት ምክንያት ደግሞ በአገሪቱ መሬት አልባ የኅብረተሰብ ክፍል (መደብ) እንዳይኖርና መሬት በጥቂቶች እጅ ብቻ የሚከማችበት ሁኔታ እንደገና እንዳይፈጠር ለመከላከል ሲባል ነው ብለው ይከራከራሉ።

4.አያይዘውም ስለመሬት ይዞታ የሚገልጸው አሁን ያለውን ሕግ አርሶአደሮች መሬታቸውን እንዳያለሙ አይከለክልም፥ ገበሬው የሚፈልገው እርዳታ እንዲደረግለት ብቻ ነው፤ የገበያውን ዘርፍ ማሻሻል ከተቻለ፤ እድገት እንዲመጣ አጋዥ የሆኑትን አገልግሎቶች ለማስፋፋት ከተቻለ የመሬቱ ሥሪት ችግር አይፈጥርም ይላሉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ምንም እንኳን የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ሥፍራ የያዘ ቢሆንም እሱን ብቻ ከሌሎቹ ነጥሎ ለማልማት ስለማይቻል የመሬት

ሥሪቱን ጥያቄ፥ የውሀውን ሃብት ልማት ጥያቄ፥የሰው ሃይል ግንባታን ማለትም ለአርሶአደሩ ሕዝብና ለሌሎቹም በተዛማጅ የሥራ መስኮች ላይ ለተሠማሩ ሠዎች በቂ ምግብ የጤና እንክብካቤና እንዲሁም መሠረታዊ ትምህርት የማግኘት ጥያቄን አብሮ ለመመለስ ሲቻል ነው አስተማማኝነትና ቀጣይነትም ባለው መንገድ የርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ሊለማና ዕድገትም ሊያስገኝ የሚችለው:: እነዚህ ሁሉ ደግሞ አምራቹ ሕዝብ ነጻነት ከሌለውና ፀጥታ ተጠብቆለትና መብቶቹም ተከብረውለት ለመኖር፥ ለመሥራት፥ ለመንቀሣቀስ፥ ለመመራመር፥ ለማሰብ፥ ለመፍጠርም ሲችል ነው ሊከናወኑ የሚችሉት:: ስለዚህ ነው ከተሣሰሩትና ከተጋመዱት ቱባ የሀገራችን ችግሮች አንደኛውን ብቻ ነጥሎ ለመፍታት እጅግ አዳጋች የሚሆነው::

ኢሕአፓ የመሬት ባለቤትነት መብት ሊኖር ይገባል የሚለውን አቋም ከመያዙ በፊት ያቀርባቸው የነበሩት ማጠየቂያዎቹ ከፍ ብለው የተጠቀሱትን ያካተቱ ነበሩ:: በኢሕአፓ ዕኑ እምነት በእርሻ ሥራና በዚያም ላይ በሚመሠረቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ ከሚተዳደረው የኢትዮጵያ ሕዝብ መጠን አኳያና የርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ኢኮኖሚ ላይ ካለው ከፍተኛ ጫና አኳያ በመመልከት፤ ወደፊት ምንም ዓይነት የመሬት ፖሊሲ ከመውጣቱ በፊት የሕዝብን ትክክለኛ ፍላጎት ለማረጋገጥ በድጋሚ አስተማማኝ ጥናቶችን ማድረግ ያሻል:: ከዚህ በላይ የመሬት ፖሊሲ መለወጥ አለበት ብሎ ኢሕአፓ ያቀረባቸው ምክንያቶችንና ሌሎችንም በማገናዘብ በድርጅቱ ውስጥና በሕዝቡም መሐከል ሌሎች ሦስተኛ አማራጭ ሊሆኑ የሚችሉም ካሉ ቀርበው በሁሉም ላይ በግልጽና አርኪ በሆነ ደረጃ አርሶአደሮችን፥ በእርሻውና በመሬት ይዞታ ዘርፍ ልዩ ጥናት ያደረጉ ጠበብትና ምሁራንን፥ የፖለቲካ ኃይሎችን፥ የሲቪክና የሙያ ማኅበራትን ያካተተና ሕዝቡን በቀጥታ ባሳተፈ መልክ ጥልቅ ውይይት በማድረግ የሰከነ አመለካከትና መግባባትንም ለመፍጠር መቻል ጠቃሚና አስፈላጊም ነው::የፖለቲካ ድርጅቶች አማራጮችን ለሕዝቡ ማቅረብ የሚጠበቅባቸው ቢሆንም ከእንግዲህ ወዲያ ግን የየራሳቸውን ዕምነት በሕዝቡ ላይ ከመጫን ሊቆጠቡ ይገባል:: ከምንም በላይ በመሬት ፖሊሲ ዘርፍ ሶስት መሰረታዊ ነጥቦች ሊዘነጉ አይገባቸውም እንላለን::

1ኛ. ወያኔ ኢህአዴግ መሬትን በእጁ በመያዝ የገበሬዉን ህይወት በቀጥታ በመቆጣጠር መሬት ለማልማት የሚያስፈልገዉን ማዳበሪያ የጸረ ተባይ ማጥፊያ መድኃኒት እየተቆጣጠረ ገበሬዉ በምርጫ ወቅት እንዲመርጠዉ የማታለያና የማስገደጃ የፖለቲካ መሳሪያ አድርጎታል:: በዚህ ሳይገታም የማልሚያና የፀረ ተባይ ማጥፊያ እዳ ያለባቸዉንም ድኃ አርሶአደሮች መሬት በመንጠቅ በማሰር ያንገላታል::

2ኛ.እስካሁን በተደረጉ ጥናቶች ከግልና ከመንግስት ባለቤትነት ወጭ ደግሞ በጋርዮሽ በደቦ የሚተዳደሩ ሰራተኞች እንዲኖሩ የጠየቁ ክፍሎች አሉ:: አብዛኞችም በአፋርና በሶማሌ የሚገኙት ዘላኖች ጥያቄያቸውም የግጦሽ መሬትን አስመልክቶ ነዉ::

3ኛ.እነ አቶ መለስ የሚፈሩት የባላባታዊ ስርዓት እንዳይመለስ ( መሬት በግል እጅ ሲገባ) ሊወሰዱ የሚችሉ ርምጃዎች አሉ፤ ለምሳሌ መሬቱን ግለሰብ ሃብታሞች ብቻ እንዳይገዙት አግዶ ማህበረሰቡ አካባቢዉን ለት/ቤት ፤ ለክሊኒክ ወይም ለስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራነት እንዲጠቀምበትና ለዚህና ለመሳሰሉ ብቻ ሽያጭ እንዲደረግ ማድረግ ይቻላል።

ለማንኛቸውም በአንዱ ወይንም በሌላው ፖለቲካዊ፥ ማኅበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ መስክ ውስጥ ያሉትን ከበድ ከበድ ያሉ ጥያቄዎች ተዛማጅነት መዘንጋት የለብንም። ከልማትና ዕድገት ጋር የተያያዙ ችግሮችን በመፍታት የሀገር ልማትና ዕድገትን ለማምጣት የሚወጣ ማንኛውም ፖሊሲና ዕቅድም በተለያዩ ሌሎች ዘርፎች ውስጥ ካሉት ተዛማጅ ችግሮች ጋር አብሮ ለመፍታት የሚቻልበትን መንገድ መሻት ያስፈልጋል እንጂ እንደሕወኃት/ኢሕአዴግ በብልጣብልጥነት ለራስ ፖሊሲ ማራመጃና መጠቀሚያ ማድረግ አገርንና ሕዝብን ከመጉዳት በቀር የሚፈይደው ነገር አይኖርም። በሌላ በኩል የወቅቱን የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ሁኔታ ስናነሳ የማይዘነጋውና ዛሬም ድረስ አጠያያቂ ሆኖ የኖረውን የውሃ ሃብታችንን ጉዳይ በጥልቀት መመርመርና መፍትሄ የመሻት ጉዳይ አንገብጋቢ እየሆነ የመጣበት ታሪካዊ አጋጣሚ ላይም ደርሰናል። ለመሆኑ የውሃ ሃብታችን ምን ያህል ነው? ምን ያህሉን ተጠቅመናል? ምን ያህሉንስ ለመጠቀም ሞክረናል? የውሃ ሃብታችን ከሃገራችን ይልቅ ማንን እየጠቀመ ነው? ለዚህና ሌሎችም ተዛማጅ የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታዎች ትንታኔ በክፍል አምስት ዝግጅታችን ብንገናኝስ?